★ ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ ★
D.N Solomon Yohannes
0911860113
0111/271609

✝

# ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የታተመው ፡ በብጹእ ዊ ፡

ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡

ዘመንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ መኃተሚያ ።
፲፱፻፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተጻፈ ።



www.ethiopianorthodox.org

በስመ፡አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አም
ላክ ፡ አሜን ።

በእግዚአብሔር ፡ ረዳትነት ፡ የጠናች ፡ የኦርቶዶክ
ሳውያን ፡ሃይማኖት ። ክብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ የሚያስረ
ዳ ፡ ምስክር ፡ እንጽፋለን ፡ ለመከራከርና ፡ ለመጣላት ፡
ብለን ፡ አይደለም ። የኢትዮጵያን ፡ ሰው ፡ ከዋቂ ፡ እ
ስከ ፡ ልጅ ፡ ሃይማኖቱ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መሠረት ፡
ላይ ፡ እንዲጠና ፡ ይረዳው ፡ ብለን ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

# ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ።

## መጀመሪያ ፡ ትምህርት ።

ጠያቂ ፡

**አንተ ፡ ልጅ ፡ ማን ፡ ፈጠረህ ።**

መላሽ ፡

**እግዚአብሔር ።**

ጠያቂ ፡

**ማን ፡ አዳነህ ።**

መላሽ ፡

**ክርስቶስ ።**

ጠያቂ ፡

**ማን ፡ ይቀድሰሃል ።**

መላሽ ፡

**መንፈስ ፡ ቅዱስ ።**

ጠያቂ ፡

**ከምን ፡ ነገር ፡ ተፈጥረሃል ።**

መላሽ ፡

**ከመሬት ።**

ጠያቂ ፡

**ከመሬት ፡ መፍጠሩ ። ምን ፡ ሊያስተምርህ ፡ ነው ።**



www.ethiopianorthodox.org

መላሽ ፡
ትሁት ፡ እንድሆንና ፡ ሞትን ፡ እንዳስብ ፡ ያስተም
ረኛል ።

ጠያቂ ፡
ስለምን ፡ ተፈጥረሽ ።

መላሽ ፡
እግዚአብሔርን ፡ እንዳመሰግነው ፡ እንድወደው ፡ እ
ንዳመልከውም ።

---

## ፪ ተኛ ፡ ትምህርት ።

ጠያቂ ፡
ይህን ፡ ዓለም ፡ ማን ፡ ፈጠረው ።

መላሽ ፡
እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ጠያቂ ፡
ከምን ፡ ፈጠረው ።

መላሽ ፡
ከሌለ ፡ በቃሉ ፡ ሁን ፡ እንዳለው ፡ ሁኖ ፡ አለ ።

ጠያቂ ፡
እግዚአብሔር ፡ በስንት ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ፈ
ጠረ ።

መላሽ ፡
በ፮ ቀን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ጠያቂ ፡
በመጀመሪያው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ፈጠረ ።

መላሽ
ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ብርሃንና ፡ መላእክትን ።



ጠያቂ ፡
በሁለተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ፈጠረ ።

መላሽ ፡
ጠፈር የሚታየው ፡ ሰማይ ፡ ማለት ፡ ነው ። በከዋክብት ፡
አስጊጦ ፡ ፈጠረው ።

ጠያቂ ፡
በ፫ ተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ፈጠረ ።

መላሽ ፡
መሬትና ፡ ውኃ ፡ ዛፍና ፡ ቡቃያ ።

ጠያቂ ፡
በ፬ ተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ፈጠረ ።

መላሽ ፡
ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብትን ።

ጠያቂ ፡
በ፭ ተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ፈጠረ ።

መላሽ ፡
ከውኃ ፡ ዓሣና ፡ ዖፍ ።

ጠያቂ ፡
በ፮ ተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ፈጠረ ።

መላሽ ፡
ከመሬት ፡ እንስሳና ፡ ሰውን ።

ጠያቂ ፡
በ፯ተኛው ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ፈጠረ ።

መላሽ ፡
ከሥራ ፡ አረፈበትና ፡ ባረከው ።

ጠያቂ ፡
፯ ተኛውን ፡ ቀን ፡ ባረከው ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ።

መላሽ ፡
በ፮ ቀን ፡ ሲፈጥር ፡ መልካም ፡ እንደሆነ ፡ አየ ፡ አ
ለ ፡ የፈጠረውን ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ መርቋልና ፡ ስ



www.ethiopianorthodox.org

ር ፡ አሜን ። የታረደው ፡ በግ ፡ የተባለው ፡ ከኛ ፡ ሥጋ
ና ፡ አጽም ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ነው ። ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ካልሆነ ፡ ይህ ፡
ሁሉ ፡ ክብርና ፡ ልዕልና ፡ እጼንት ፡ ተሰጠው ። አየህን ፡
እንዳልኩህ ፡ በግ ፡ የተባለው ፡ ትስብእት ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡
አንድ ፡ ክብር ፡ ሲቀበል ፡ በተዋህዶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡
ካልሆነማ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ክብርና ፡ ልእልና ፡ ለመለኮት ፡
ብቻ ፡ የሚገባ ፡ ከሆነ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሰማይ ፡ ሠራዊት ፡
በግ ፡ ለተባለው ፡ ትስብእት ፡ ለምን ፡ አቀረቡለት ። በተ
ዋህዶ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ። የታረደው
ም ፡ በግ ፡ እርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ። ቤተክርስቲያ
ንን ፡ በደሙ ፡ የዋጃት ፡ እርሱም ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፡ በመ
ስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡ በደሙ ፡ የዋጀን ። እንዲህ ፡ ካልሆነ ፡
ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዴት ፡ ደፍሮ ፡ ትስብእትን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ነው ፡ አለ ። ደሙንስ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ደም ፡ ነው ፡ እንዴት ፡ አለው ። የታረደውም ፡ በግ ፡ የተ
ባለው ፡ ኢየሱስ ፡ አምላክ ፡ ካልሆነ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡
አንድ ፡ ፈቃድ ። አንድ ፡ ሥራ ። ከዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ከተቀ
መጠው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ክብር ፡ እንዴት ፡ ይከብራል ።
አንድስ ፡ ካልሆነ ፡ መድኀኒት ፡ በዙፋኑ ፡ ለተቀመጠና ፡
ለበጉ ፡ ማለቱን ፡ ትቶ ፡ ለልጁ ፡ አይልም ፡ ኑሮዋልን ።
ካሕናተ ፡ ሰማይ ፡ እስኪሰግዱለት ፡ ድረስ ፡ ፩ ባሕርይ ፡ ካ
ልሆነ ፡ መድኀኒት ፡ በዙፋኑ ፡ ለተቀመጠውና ፡ ለበጉ ፡
ማለትን ፡ ትቶ ፡ ለልጁ ፡ አይልም ፡ ኑሮዋልን ። ካሕናተ ፡
ሰማይ ፡ እስኪሰግዱለት ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ካል
ሆነ ፡ ማለትን ፡ ትቶ ፡ ለተቀመጠውና ፡ ለቅድመ ፡ ዓለ
ም ፡ ልጁ ፡ አይልም ፡ ኑሮዋልን ።

ጠያቂ ፡

የዚህን ፡ መሰል ፡ ምሥክር ፡ እንዳለህ ፡ አስረዳኝ ።

መላሽ ፡



ይኸው ፡ ራዕይ ፡ ም ፡ ፯ቁ ፱ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አየሁ ፡
እነሆ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ለማንም ፡ ይቈጥራቸው ፡ ዘንድ ፡
የማይቻለው ። ከአሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ከወገኑም ፡ ከነገዱም ፡
ከቋንቋችም ፡ በዙፋኑ ፡ ፊት ፡ ቁመው ፡ በበጉ ፡ ፊት ። ነ
ጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ የሰሌንም ፡ ዝንጣፊዎች ፡ ይዘ
ው ፡ በታላቅ ፡ ቃልም ፡ ጮሁ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ። መድኀ
ኒት ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠውና ፡ ለበጉ ፡ አለ ። ቁ
፲ ፡ ከዙፋኑ ፡ ላይ ፡ የተቀመጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡
ነው ። በግ ፡ የተባለው ፡ የኛን ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ኢየሱስ
ነው ። ቃልና ፡ ትስብእት ፡ በተዋህዶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡
ካልሆነ ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ክብር ፡ ትክክል ፡ እንዴት ፡ ሰጡ
ት ። ደግሞ ፡ ቁ ፡ ፲፬ ልብሳቸውን ፡ አጸቡ ፡ አነጹትም ፡
በበጉ ፡ ደም ፡ አለ ። በግ ፡ የተባለ ፡ ኢየሱስ ፡ ከቃል ፡ ጋ
ራ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ካልሆነ ፡ ደሙ ፡ የሰውን ፡ ልብስ ፡
እንዴት ፡ ያነፃል ። የሰው ፡ ደም ፡ ያሳድፋል ፡ እንጂ ፡ እ
ንዴት ፡ ያነፃል ። በተዋህዶ ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡ ማለቱ ፡ የቱ
ሳኔና ፡ የመቀላቀል ፡ የመደባለቅ ፡ አይደለም ። እንደ ፡
ሥጋና ፡ እንደ ፡ ነፍስ ፡ አንድነት ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
የወልድ ፡ ትስብእት ፡ ከመለኮት ፡ ጋራ ፡ ፩እንደሆነ ፡ ሲያ
ስረዳ ፡ በቁ፡ ፲፯ በዙፋኑ ፡ መሃከል ፡ ያለው ፡ በግ ፡ ያሠማ
ራቸዋል ፡ አለ ። ኢየሱስ ፡ ከቃል ፡ ጋራ ፡ በተዋህዶ ፡ አ
ንድ ፡ ባሕርይ ፡ ካልሆነ ፡ ከዙፋኑ ፡ መካከል ፡ እንዴት ፡
ይሆናል ። አምላክና ፡ ሰው ፡ ካሉ ፡ ለአምላክ ፡ አንድ ፡
ሥራ ። ለሰው ፡ አንድ ፡ ሥራ ፡ ለይተውስ ፡ ከሰጡ ። አ
ምላክ ፡ አልሆነም ፡ ላሉት ፡ ሰው ፡ መንበረ ፡ ጸባዖትን ፡
ማን ፡ ይሰጠዋል ። ደሙስ ፡ ልብሳቸውን ፡ አጽቦ ፡ እን
ዴት ፡ ያነፃዋል ። ኀጢአትን ፡ የሚያነፃ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡
እንጂ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አን
ድ ፡ ሥራ ፡ ካልሆነ ። እንዴት ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ለዘለዓለ
ሙ ፡ ይነግሣል ፡ እንደተባለ ፡ ፯ ተኛው ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፡ በ



www.ethiopianorthodox.org

ሀ ፡ አለ ። ያም ፡ ያመሰግነኛል ፡ ከኔ ፡ ይወስዳልና ፡ ይነግራችሁማል ። ያለውን ፡ ቃል ፡ ይዘው ። ከወልድ ፡ እንዲሠርፅ ፡ ያስረዳል ፡ ይላሉ ።

መላሽ ፡

አስቀድሜ ፡ እንደጻፍኩልህ ፡ ሥላሴ ፡ ከባሕርዩ ፡ ሁለት ፡ ሥራ ፡ አለው ። አንደኛው ፡ ያካላት ፡ ሥራ ፡ ነው ። መውለድ ፡ መወለድ ። መሥረፅ ፡ ይባላል ። ከዚሁ ፡ ያንዱ ፡ አካል ፡ ሥራ ፡ ካንዱ ፡ አካል ፡ አይተላለፍም ። ይተላለፋል ፡ ቢሉ ። አብ ። አብ ፡ ብቻ ፡ መባሉን ፡ ቀርቶ ፡ ወልድ ፡ ይሆናል ። ወልድም ። ወልድ ፡ ብቻ ፡ ሁኖ ፡ አይቀርም ፡ አብ ፡ ይሆናል ። ራሱን ፡ በራሱ ፡ ይወልዳል ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እንደነሱ ፡ እምነት ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ ይሆናል ። ራሱን ፡ በራሱ ፡ ያሠርፃል ። እንግዴሀ ፡ ሥላሴ ፡ ሶስት ፡ አካል ፡ መሆኑ ፡ ይቀርና ፡ ዘጠኝ ፡ አካል ፡ ሊሆንባቸው ፡ ነው ። ይህም ፡ ታላቅ ፡ ክሕደት ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ቀድም ፡ ክርስቲያን ፡ የተባለ ፡ ሁሉ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያመነበት ፡ የለም ።

ጠያቂ ፡

ሥላሴ ፡ ሁለተኛ ፡ ግብር ፡ አለው ፡ ያልከው ፡ እንደምንድር ፡ ነው ።

መላሽ ፡

ሶስቱ ፡ አካላት ፡ ክብር ፡ ይግባቸው ፡ ባንድ ፡ ሁነው ፡ አብ ፡ የሚሠራውን ፡ ወልድ ። ወልድ ፡ የሚሠራውን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚሠራውን ፡ አብና ፡ ወልድ ፡ የሚሠሩት ፡ ግብር ፡ ይህ ፡ ነው ። መፍጠር ። መግደል ። መሥጠት ። መንሣት ። መጠበቅ ። ማሣለፍ ። ነው ። ይህነን ፡ ቃል ፡ እንድትረዳው ፡ ጌታ ፡ በዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቁ ፡ ፲ እንዲህ ፡ አለ ። ለኔ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ላንተ ፡ ነው ። ያንተውም ፡ እርሱ ፡ ለኔ ፡ ነው ፡ ካለ ፡ በኋላ ። ቅዱስ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ በስምህ ፡ ጠ



ብቃቸው ፡ እሊህ ፡ የሰጠኸኝን ፡ አንድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደኛ ፡ ብሎ ፡ ተረጐመ ። በም ፡ ፲፮ ፡ ቁ ፡ ፲፪ ብዙ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ የምነግራችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ አትችሉትም ፡ ዛሬ ፡ ትሸከሙት ፡ ዘንድ ፡ ካለ ፡ በኋላ ። ያም ፡ የውነት ፡ መንፈስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ መንገድ ፡ ይመራችኋል ። ከርሱ ፡ አይናገርምና ፡ የሚሰማውን ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ። የሚመጣውን ፡ ሁሉ ፡ ይገልጥላችኋል ። ያም ፡ ያመሰግነኛል ፡ ፪ ከኔ ፡ ወስዶ ፡ ይነግራችሁማል ፡ ማለቱ ። እንደባሕርዩ ፡ ስለ ፡ ሆነ ። አንድ ፡ የምንሆንበት ፡ የዕውቀት ፡ መዝገብ ፡ አለንና ። ዛሬ ፡ የማትችሉት ፡ በጰንጠቆስጤ ፡ ቀን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ባደረባችሁ ፡ ጊዜ ። ከነገሥታት ፡ ከመኳንንት ፡ ፊት ፡ ቁማችሁ ፡ የወንጌልን ፡ የምስራች ፡ ለአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ፍርሃት ፡ ትነግራላችሁ ፡ ሲል ፡ ነው ። ክቡር ፡ ጠያቂዬ ፡ ሆይ ። ጌታ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከራሱ ፡ አይናገርም ። ግን ፡ ከኔ ፡ ወስዶ ፡ ይነግራችሁማል ፡ ሲል ፡ ጊዜ ። እንዴት ፡ ከርሱ ፡ ሠረፀ ፡ ይሉታል ። ነገር ፡ ማለት ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ከአፉ ፡ ወጥቶ ፡ ወዲያው ፡ እንደተሰማ ፡ ይጠፋል ፡ እንጂ ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እንዲዚሁ ፡ ነው ፡ ካሉት ። እንደ ፡ መቅዶንዮስ ፡ ፍጡር ፡ ነው ፡ ማለታቸው ፡ አይደለምን ።

ጠያቂ ፡

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ እንደሠረፀ ፡ ሌላ ፡ ምሥክር ፡ አለህን ።

መላሽ ፡

አዎን ፡ የማይናወጥ ፡ ምስክር ፡ አለኝ ። ጌታ ፡ በማቴዎስ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቁ ፡ ፳፯ እንዲህ ፡ አለ ። ማንም ፡ ወልድን ፡ አያውቀውም ፡ ከአብ ፡ በቀር ። አብንም ፡ ማንም ፡ አያውቀውም ፡ ከወልድ ፡ በቀር ። እንዲህ ፡ የተናገረ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ አብ ፡ ብቻውን ፡



www.ethiopianorthodox.org

መሠረት ፡ እንደሆነ ፡ ሊያስረዳ ። በዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቁ ፡ ፳፰ ከአብ ፡ ወጣሁ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መጣሁ ፡ አለ ። ከአብ ፡ ብቻ ፡ መወለዱን ፡ እንዳስረዳን ፡ እንዲሁ ፡ የሚያጸና ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ግን ፡በመጣ ፡ ጊዜ ። እኔም ፡ ለላንት ፡ የምሰደው ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ የውነት ፡ መንፈስ ፡ ከአብ ፡ የሚወጣ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መሠከረ ። ከአምላክ ፡ ምስክርነት ፡ ወዲህ ፡ የማንን ፡ ምሥክርነት ፡ እንቀበላለን ። የስማይ ፡ መምሕራችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። አባቱን ፡ በባሕርይ ፡ እውቀት ፡ የሚያውቅ ፡ እኔ ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ ወጣሁ ፡ እንዳለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ ሠረፀ ፡ ብሎ ፡ ከመሠከረ ፡ በኋላ ። እናባ ፡ ዮሐንስ ፡ የአምላክን ፡ ቃል ፡ ጥሰው ፡ ያለቆቻቸውን ፡ ግዝትና ፡ ርግማን ፡ አፍርሰው ። የሊቃውንቶቻቸውን ፡ ቃል ፡ቢጠ ቅሱ ፡ ማን ፡ ይሰማቸዋል ። ካልተማረና ፡ ከደንቆሮ ፡ ሰው ፡ በቀር ። የተረሳ ፡ ጥቅስ ፡ ሁለት ፡ መስመር ፡ ይችላል ። የሰው ፡ ምሥክር ፡ ከመቀበል ። የእግዚአብሔር ፡ ምሥክርነት ፡ እጅግ ፡ ይበልጣል ። ፩ ዮሐንስ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቁ ፡ ፱ ደግሞ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ መሥረፁን ፡ በጣም ፡ እንድትረዳ ። ሶስት ፡ ምሥክር ፡ አመጣልሃለሁ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማይታበል ፡ ቃሉ ፡ እንዳስተማረን ፡ የሃይማኖታችን ፡ አለቃ ፡ ወሰኝ ፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ አንደኛው ፡ ምሥክር ። እኔ ፡ አብን ፡ እለምናለሁ ። ሌላ ፡ የሚያጸና ፡ ይሰጣችኋል ። ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለም ። ዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቁ ፲፮ ።

ሁለተኛው ፡ የሚያጸና ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አብ ፡ በስሜ ፡ የሚሰደው ፡ እርሱ ፡ ሁሉንም ፡ ያስተምራችኋል ፡ ያልኋችሁን ፡ ሁሉ ፡ ያሳስባችኋል ፡ አለ ። ቁ ፡ ፳፮ ሶስተኛውም ፡ የሚያጸና ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ግን ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ የውነት ፡ መንፈስ ፡



ከአብ ፡ የሚሠርፅ ፡ እርሱ ፡ ስለኔ ፡ ይመሠክራል ። ዮሐንስ ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ቁ ፡ ፳፮ ይኸው ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ጌታችን ፡ መድኀኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመጀመሪያ ፡ ምሥክርነቱ ። ከአብ ፡ የጰራቅሊጦስን ፡ ጸጋ ፡ ለመስጠት ፡ እንደለመነ ፡ ገለጠ ። አካል ፡ አይሰጥምና ። በሁለተኛው ፡ ምሥክር ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መላክ ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ መሠከረ ። በሶስተኛው ፡ ምሥክርነቱ ፡ የዘለዓለም ፡ መሥረፁን ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነ ፡ አስረዳን ። በዚሁ ፡ በሶስቱ ፡ ምሥክርነትና ፡ ባለፈውም ፡ ጥቅስ ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖትን ፡ ለፈለገ ፡ ሰውና ። የአምላኩን ፡ ቃል ፡ ለመስማት ፡ ለተዘጋጀ ፡ ሰው ። ይኸ ፡ ይበቃዋል ።

## ክፍል ፡ ስለ ፡ ነፍስ ፡ መገኘት ።

ጠያቂ ፡

የሰው ፡ ነፍስ ፡ ከወዴት ፡ ትፈጠራለች ።

መላሽ ፡

በእግዚከብሔ ፡ ትእዛዝ ፡ ካባትና ፡ ከናት ፡ ትፈጠራለች ። እግአብሔር ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ ከፈጠረ ፡ በኋላ ። ብዙ ፡ ተባዙም ፡ ምድርንም ፡ ምሏት ፡ ብሎ ፡ መረቃቸው ። ይኸቺ ፡ ምርቃት ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ትኖራለች ። ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ም ፡ ፲፯ ፡ ቁ ፳፮ እንዲህ ፡ አለ ። እሱም ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ፈጠረ ። በምድር ፡ ፊት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አለ ። እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ ሥጋን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ነፍስን ፡ ጭምር ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ጠያቂ ፡

ካቶሊኮች ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍስን ፡ እምኅበ ፡ አልቦ ፡ ከፈጠረ ፡ በኋላ ። ባባትና ፡ በናት ፡ ምክን



www.ethiopianorthodox.org

በትም ፡ አያፍርም ። ባ ፩ ቆሮንቶስ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቁ ፡ ፬ ያን
ንም ፡ መንፈሳዊ ፡ አንድ ፡ መጠጥ ፡ ሁሉ ፡ ጠጡ ፡ ከርሳ
ቸው ፡ ጋራ ፡ ይከተል ፡ ከነበረው ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ደንጊ
ያ ፡ ጠጥተዋልና ፡ ያም ፡ ደንጊያ ፡ ክርስቶስ ፡ ነበረ ፡ አ
ለ ። ይህ ፡ የተቀደሰ ፡ ምሥክር ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲ
ያንና ፡ የሃይማኖታችን ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ነው ። እር
ሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲለን ፡ ጊዜ ፡ ለምዕመና
ን ፡ ሕይወት ። ለከሐድያን ፡ ጥፋት ። እርሱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡
ሲለን ፡ ጊዜ ። እንዴት ፡ ብለን ፡ ተመልሰን ፡ ጴጥሮስን ፡
የሃይማኖታችን ፡ መሠረት ፡ ደንጊያ ፡ ሆን ፡ እንላለን ።
አንተ ፡ ደንጊያ ፡ ነህ ፡ ለምን ፡ አለው ፡ ብለህ ፡ ብትጠይ
ቀኝ ። እርሱ ፡ ሰውነቱ ፡ ተለውጦ ፡ ደንጊያ ፡ ሆን ፡ ተብ
ሎ ፡ አይደለም ። በጌታ ፡ ፊት ፡ የታመነበት ፡ የጸና ፡ ሃ
ይማኖት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ። ያውም ፡ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡
የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነህ ፡ ያለውን ፡ ነው ።
ይህነን ፡ ማለታችን ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ ጠልተን ፡ አይ
ደለም ። አባታችንም ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቶ ፡ አይደለም ። ወ
ራሾቹ ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ አለቅነት ፡ እንደሌላቸው ፡ ለማሳ
ወቅ ፡ ነው ። ዋና ፡ መሠረት ፡ ክርስቶስ ፡ ሁኖ ፡ ሲያበቃ ፡
ጴጥሮስ ፡ ሁለተኛ ፡ መሠረት ፡ ሆን ፡ ማለታቸው ፡ ለክር
ስቶስ ፡ አካፋይ ፡ ማድረጋቸው ፡ ነውን ። ወይስ ፡ ያግዘዋ
ል ፡ ማለት ፡ ነውን ። በክርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ ለዓለም ፡ መ
ምሕርነት ፡ የተሾመው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በኤፌሶን ፡
መልእክት ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቁ ፡ ፳ የክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ
ከጴጥሮስ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ እንዳልተሠራች ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡ ያስተምረናል ። ከሐዋርያትና ፡ ከነቢያት ፡ መሠ
ረት ፡ ላይ ፡ ተሰርታችኋል ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መሠ
ረት ፡ ላይ ፡ እርሱ ፡ የማዕዘን ፡ ራስ ፡ የሆን ። ደግሞ ፡ ባ ፩
ቆሮንቶስ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቁ ፲፩ ማንም ፡ አይችልምና ፡ ሌላ ፡
መሠረት ፡ ይመሠርት ፡ ዘንድ ። ከዚያው ፡ ከተመሠረተ



ው ፡ በቀር ። እርሱም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ቅዱ
ስ ፡ ጳውሎስም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መሠረትነት ፡
በቀር ። ሌላ ፡ መሠረት ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ሲነግረን ፡ ጊዜ ፡
ደፍረው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ቃል ፡ ጥሰው ። ጴጥሮ
ስ ፡ በክርስቶስ ፡ ፈንታ ፡ መሠረት ፡ ሆን ፡ ማለታቸውን ፡
ልብ ፡ አድርግ ። በሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቁ ፡ ፲፪ በ
ማንም ፡ ደህንነት ፡ የለም ፡ በሌላው ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ የለም
ና ። በሰማይ ፡ ታች ፡ ለሰው ፡ የተሰጠ ፡ ይድን ፡ ዘንድ ፡ የ
ሚገባ ፡ አለ ። እኛ ፡ የምንድንበት ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶ
ስ ፡ ሃይማኖት ፡ መሠረትነት ፡ ነው ። በሌላ ፡ በሚሠበር ፡
መሠረት ፡ እንድናለን ፡ ብለን ፡ ከንቱ ፡ ተስፋ ፡ እንዴ
ት ፡ እናደርጋለን ። ፍጡርን ፡ አቅፈን ፡ ፈጣሪን ፡ ብንነ
ቅፍ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ክህደት ፡ ይሆንብናል ።

ጠያቂ ፡

በሉቃስ ፡ ም ፡ ፳፪ ፡ ቁ ፴፩ ጌታ ፡ አለ ። ስምዖን ፡ ስ
ምዖን ፡ እነሆ ፡ ሰይጣን ፡ በላንት ፡ ተመኘ ፡ ሊነፋችሁ ፡
እንደ ፡ ስንዴ ። እኔ ፡ ግን ፡ ስላንተ ፡ ለመንሁ ፡ ሃይማኖ
ትህ ፡ እንዳይጠፋ ። አንተም ፡ በተመለስክ ፡ ጊዜ ፡ ወን
ድሞችህን ፡ አጽና ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ይዘው ። ጴጥሮስ ፡
የሐዋርያት ፡ አለቃ ፡ ነው ። ወራሾቹም ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት ፡ እንሆናለን ፡ ይላሉ ። ይህ ፡ እውነት ፡ ነውን ፡
ወይስ ፡ ሐሠት ።

መላሽ ፡

ይህ ፡ ዋና ፡ ሐሠት ፡ ነው ። ኮቶሊኮች ፡ ለራሳቸው ፡
መክበሪያ ፡ ብለው ፡ ነው ፡ እንጂ ። ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡
አስበው ፡ አይደለም ። እርሱ ፡ ራሱ ፡ እንኳ ፡ ጌታው ፡
ሲናገር ፡ የሰማ ። አለቃ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ አላሰበም ። ይኸነ
ኑ ፡ በመጀመሪያ ፡ መልእክቱ ፡ ም ፡ ፭ ቁ ፬ እንዲህ ፡ ሲ
ል ፡ ተርጉሞታል ። የጠባቆች ፡ አለቃ ፡ በተገለጠ ፡ ጊ
ዜ ። የማይጠፋውን ፡ የክብርን ፡ አክሊል ፡ ትወስዳላች



www.ethiopianorthodox.org

አህያውን ፡ ይልቅ ፡ እናከብር ፡ ቢሉ ፡ አይገባም ። እኛ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆን ፡ ሁሉ ፡ ኦ፲፱መስቀል ፡ ላይ ፡ በመሰቀሉ ፡ ድነናል ፡ እንጂ ። በህያው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ስለ ፡ ከበረ ፡ አልዳንም ። ስለዚህ ፡ መስቀልን ፡ እናከብረዋለን ።

ጠያቂ ፡

ለመስቀል ፡ ሌላ ፡ ስም ፡ አለውን ።

መላሽ ፡

አዎን ፡ አክሊል ፡ ይባላል ፡ ሰሎሞን ፡ እንዳለው ። በመሐልይ ፡ ምዕ ፡ ፫ ፡ ቁ ፡ ፲፩ እናንተ ፡ የጽዮን ፡ ልጆች ፡ ውጡ ፡ ለንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ እናቱ ፡ በሰርጉ ፡ ቀንና ፡ በልቡ ፡ ደስታ ፡ ቀንም ፡ ያደረገችለትን ፡ አክሊል ፡ እዩ ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ በዓለም ፡ የከበሩ ፡ የክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ መስቀል ፡ የክርስቶስ ፡ ዘውድ ፡ እንደሆነ ፡ አውቀው ፡ ከዘውዳቸው ፡ አክብረው ፡ ከከበረው ፡ ዕንቍ ፡ ላይ ፡ ያስቀምጡታል ።

ጠያቂ ፡

የሐዋርያት ፡ ሶስተኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ንገረኝ ።

መላሽ ፡

ሶስተኛው ፡ ትእዛዝ ፡ ኑዛዜ ፡ ነው ፡ የሠራነው ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ትንሽ ፡ ተብሎ ፡ እንዳይናቅ ፡ ትልቅ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ታፍሮ ፡ እንዳይሸሸግ ፡ ለታመነ ፡ ቄስ ፡ ያለማፈር ፡ ገልጦ ፡ መናገር ፡ ይገባል ።

ጠያቂ ፡

ጌታ ፡ ይህን ፡ ለቄስ ፡ በኃጢአት ፡ መናዘዝ ፡ አዚልን ።

መላሽ ፡

አዎን ፡ ለሐዋርያት ፡ የክህነት ፡ ሥልጣን ፡ በሰጣቸው ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ። ኃጢአቱን ፡ የተዋችሁለት ፡ ቀረችለት ። የያዛችሁበትም ፡ ሰው ፡ ተያዘችበት ፡



አላቸው ። ዓቃቤ ፡ ሥራይ ፡ የታመመውን ፡ ሰው ፡ ደዌውን ፡ ካላወቀ ፡ መድኃኒት ፡ መስጠት ፡ አይቻለውም ። እንደዚሁ ፡ የሐዋርያት ፡ ተከታዮች ፡ ቀሳውስት ፡ ሰው ፡ የሠራውን ፡ ኃጢአት ፡ ለይቶ ፡ ካልነገራቸው ፡ ኃጢአት ፡ ለመፍታት ፡ አይሆንላቸውም ።

ጠያቂ ፡

ይህ ፡ ኑዛዜ ፡ ከጥንት ፡ የመጣ ፡ ነውን ። ወይስ ፡ አዲስ ፡ ነው ።

መላሽ ፡

ከጥንት ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ አዲስ ፡ አይ ደለም ። እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዘው ። በሌዋውያን ፡ ምዕ ፡ ፭ ፡ ቁ ፡ ፬ መሃላ ፡ የማለች ፡ ነፍስ ፡ ክፉም ፡ ሆነ ፡ መልካምም ፡ ሆነ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ሲያስብ ፡ እንዲምል ፡ ቢሰውራትም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ ቢታወቅ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በደለኛ ፡ ሆነች ። ከለዚያ ፡ ባንዳቸው ፡ ሰው ፡ ኃጢአት ፡ ቢሠራ ፡ ኃጢአቱን ፡ ይናዘዝ ፡ አለ ። ደግሞ ፡ ሰሎሞን ፡ በምሳሌ ፡ ምዕ ፡ ፳፰ ፡ ቁ ፲፫ ኃጢአቱን ፡ የሚሠውር ፡ ደህንነት ፡ አይሆንለትም ፡ የሚናዘዝባትና ፡ የሚተዋት ፡ ግን ፡ ምሕረት ፡ ያገኛል ፡ አለ ። ደግሞ ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕ ፡ ፫ ፡ ቁ ፡ ፮ እንዲህ ፡ አለ ፡ በዮርዳኖስም ፡ ይጠመቁ ፡ ነበሩ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ እስታውቀው ፡ አለ ።

ጠያቂ ፡

የሐዋርያትን ፡ አራተኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ንገረኝ ።

መላሽ ፡

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ክቡር ፡ ሥጋና ፡ ደሙን ፡ መቀበል ፡ ነው ። ያቀባበሉን ፡ ውል ፡ ግን ፡ ከሰባቱ ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር ፡ ላይ ፡ እጽፍልሃለሁ ።

ጠያቂ ፡

አምስተኛና ፡ ስድስተኛውን ፡ ትእዛዝ ፡ ንገረኝ ።



www.ethiopianorthodox.org

ው ፡ ፈርተው ፡ ይጠመቁ ፡ ብለው ፡ አዘዙ ። ስለምን ፡ ቢሉ ፡ ጌታ ፡ በማይታበል ፡ ቃሉ ፡ እውነት ፡ እውነት ፡ እልሃለሁ ፡ ማንም ፡ ከውኃና ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ካልተወለደ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡ ስለዚህ ፡ ሕፃናት ፡ ይጠመቁ ፡ ብለው ፡ ሐዋርያትም ፡ ሊቃውንትም ፡ አዘዙ ። ዮሐንስ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቁ ፡ ፭ ።

ጠያቂ ፡

የሜሮን ፡ ምሥጢር ፡ እንደምንድነው ።

መላሽ ፡

የተቀደሰ ፡ ቅብዕ ፡ ነው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥራ ፡ የሚጠመቅ ፡ ሰው ፡ በውጭ ፡ ሰውነቱ ፡ ሲቀባ ፡ ሃይማኖቱ ፡ እንዲጸና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያድርበታል ። ጽላትና ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማገልገል ፡ እንዲለዩ ፡ ይቀቡበታል ።

ጠያቂ ፡

የዚህን ፡ የሜሮን ፡ መቀባት ፡ ሐዋርያት ፡ ያዘሉን ።

መላሽ ፡

አዎን ፡ ሐዋርያ ፡ በመጀመሪ ፡ መልእክቱ ፡ ም ፡ ፪ ፡ ቁ ፡ ፳ እንዲህ ፡ አለ ። እናንተም ፡ መቅባት ፡ አላችሁ ፡ ከቅዱሱ ፡ ሁሉንም ፡ አውቃችኋል ። ደግሞ ፡ አለ ፡ ከርሱ ፡ የወሰዳችኋትም ፡ መቅባት ፡ በናንተ ፡ ትጸናባችኋለች ፡ ማንም ፡ ያስተምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ አትሹም ፡ እንደዚሁ ፡ መቅባት ፡ ያስተምራችኋል ፡ እንጂ ። ስለ ፡ ሁሉ ፡ እርሱም ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፡ ሐሡትም ፡ አይደለም ፡ እንዳስተማራችሁም ፡ ትጸኑበታላችሁ ። ቁ ፡ ፳፯ ደግሞ ፡ ጳውሎስ ፡ በ ፪ ቆሮንቶስ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቁ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ እግዚአብሔር ፡ የሚያጸናን ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ በክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ የቀባን ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ አተመን ፡ የመንፈሱንም ፡ መያዣ ፡ በልባችን ፡ ሰ



ጠን ፡ ብሏል ።

ጠያቂ ፡

የሜሮን ፡ መቀባት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተጀመረ ።

መላሽ ፡

በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ነው ። አስተምረው ፡ ሲያጠምቁ ፡ እጃቸውን ፡ በጫኑ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይወርድ ፡ ነበር ። ስብከት ፡ ከሰፋ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሐዋርያት ፡ አገሩን ፡ ሁሉ ፡ እየዞሩ ፡ የተጠመቀውን ፡ ሁሉ ፡ እጃቸውን ፡ ለመጫን ፡ የማይቻላቸው ፡ ቢሆን ፡ ቅብዓ ፡ ሜሮንን ፡ በአንብሮ ፡ እድ ፡ ፈንታ ፡ ይሁን ፡ ብለው ፡ አዘዙ ።

ጠያቂ ፡

ምሥጢረ ፡ ቁርባን ፡ እንደ ፡ ምንድን ፡ ነው ።

መላሽ ፡

የቁርባን ፡ ምሥጢር ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅዱስ ፡ ስጋው ፡ ደሙ ፡ ነው ። ለምዕመናን ፡ በቸርነቱ ፡ የሰጣቸው ፡ በሕብስትና ፡ በወይን ፡ መልክ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

ጠያቂ ፡

ጌታ ፡ ሥጋዬን ፡ ብሉ ፡ ደሜን ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ አዘናልን ።

መላሽ ፡

አዎን ፡ አጥብቆ ፡ በብርቱ ፡ ትእዛዝ ፡ አዘናል ። እ እንዲህ ፡ ሲል ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ የሕይወት ፡ እንጀራ ፡ አባቶቻችሁ ፡ መና ፡ በሉ ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ ሞቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከሰማይ ፡ የወረደው ፡ እንጀራ ፡ ከርሱ ፡ የሚበላ ፡ ሁሉ ፡ እንዳይሞት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ሕያው ፡ እንጀራ ፡ ከሰማይ ፡ የወረድኩ ፡ ማንም ፡ ከዚህ ፡ እንጀራ ፡ የበላ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ እኔ ፡ የምሰጠው ፡ እንጀራ ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ እሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ያለኝ ። አይሁድም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተከራከሩ ፡ እን



www.ethiopianorthodox.org

ስከ ፡ ፍርድ ፡ ቀን ፡ ድረስ ። ሥጋ ፡ ግን ፡ ከተፈጠረበት ፡ መሬት ፡ ፈርሶ ፡ ይቈያል ። ነፍስም ፡ በትንሣኤ ፡ ከሥጋዋ ፡ ጋራ ፡ ከተዋሃደች ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ሥራዋ ፡ ዋጋ ፡ ትቀበላለች ፡ መልካም ፡ ሠርታ ፡ ብትገኝ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ትወርሳለች ። የወንጌልን ፡ ቃል ፡ አፍርሳ ፡ ሥጋዋ ፡ አሸንፏት ፡ የሥጋዋን ፡ ፈቃድ ፡ ሠርታ ፡ ብትገኝ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ተፈርዶባት ፡ ዘለዓለም ፡ ስትሳቀይ ፡ ትኖራለች ።

ጠያቂ ፡

ትንሣኤ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ።

መላሽ ፡

ትንሣኤ ፡ ማለት ፡ ነፍስ ፡ በፈጣሪዋ ፡ ፈቃድና ፡ ኃይል ፡ ከጥንት ፡ ሥጋዋ ፡ ተመልሳ ፡ ትዋሃድና ፡ ለፍርድ ፡ መቀበል ፡ ተጠንቅቀው ፡ ይቈያሉ ።

ጠያቂ ፡

ፍርድ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ።

መላሽ ፡

ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ ከክርስቶስ ፡ መንበር ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አይቀርለትም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍርድ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ። ጻድቃንን ፡ በቀኙ ፡ ኃጥአንን ፡ በግራው ፡ አቁሞ ፡ ልቡና ፡ የሸሸገውን ፡ ሁሉ ፡ ገልጦ ፡ በውነት ፡ ፍርድ ፡ በሥጋ ፡ እንደሠራነው ፡ ሥራ ፡ ይፈርድብናል ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጻድቃን ፡ ብርሃን ፡ ተሸልመው ፡ የዘለዓለምን ፡ ክብር ፡ ይወርሳሉ ። ኃጥአንም ፡ ሐፍረት ፡ ለብሰው ፡ ገሃነም ፡ ተፈርደባቸው ። ፈቃዱን ፡ ከሠሩለት ፡ ከሰይጣን ፡ ጋራ ፡ ዘለዓለም ፡ ሲሳቀዩ ፡ ይኖራሉ ።



አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ አምላክ ። ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይገባው ፡ አሜን ። ከሁን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ድረስ ፡ አሜን ።

ለዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘአጽሐፎ ፡ ወዘአውጽኦ ፡ እምብሉይ ፡ ወሐዲስ ። ብላታ ፡ ጳውሎስ ፡ ዘብሔረ ፡ ግብፅ ።

ወዘ ፡ ጸሐፎ ፡ ካሳሁን ። በ ፲ ወ ፱፻ ወ ፫ ዓመተ ፡ ምሕረት ። በወርኃ ፡ ሚያዝያ ፡ በ ፳፯ ቀን ፡ ተጻፈ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ።

ዲያቆን ሰሎሞን
D/N Solomon

የኢትዮጵያ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ መኃተሚያ ።



www.ethiopianorthodox.org